ለኢህአዴግ አንድ ወጥ የሆነ አመጻኛ የትግል ስልት ሃቀኛና ሁለገብ አጸፋ መስጠት ስለሚችሉ የህዝባችንን የመከራ ዘመን ለማሳጠር ታሪክ የማይረሳው አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይቆጠራል።

# የእብዶች ሎጅክ

የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት አስሪ አምስት ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስት ጋዜጦች ከህትመት ውጭ እንዲሆኑ ከማድረግ አልፎ በነጻው ፕሬስ ላይ ቀደም ሲልም ተያይዞት የነበረውን የመንግሥታዊ ሽብር ዘመቻ ወደ አዲስ ምእራፍ አሸጋግሮ የጋዜጦችን ጽ/ቤትና ንብረት በእሳት እስከማጋየት ደርሷል።

ወያኔ ወደዚህ አዲስ የሽብር ስልት ለምን እንደተሸጋገረ ብዙ ታዛቢዎች ግራ ተጋብተዋል። ይህም ሆኖ ከአርብ ማታ ወዲህ ተደጋግመው የሚመጡ ሁለት ምክንያቱች አሉ። በአንድ በኩል የሀገሪቱ ውስጣዊ የፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታ ሲሆን ሌላው ደግሞ በመጋቢት አጋማሽ የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ያደርጋሉ የተባለው ጉብኝት ጋር ያያይዙታል። እነዚህ ምክንያቶች በርግጥም እውነት ከሆኑ የወያኔ መሪዎች የተከተሉት የእብዶች ሎጅክ ነው ማለት ይቻላል።

የሃገሪቱን ውስጣዊ ሁኔታ ምክንያትንት እንመልከት። ርግጥ ዛሬ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ እየሆነ የመጣው በአንድ በኩል በወያኔ በራሱ ውስጥ ያለው ቅራኔና በሌላ በኩል ደግሞ ከእለት እለት እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለው ጸረ ወያኔ የሆነው የተቃዋሚ ኃይሎች ሁለገብ ትግል አለ። ይህ እንደምክንያት ከተወሰደ በእርግጥም ህዝቡ ከሚጠረጥረውና ታዛቢዎች ከሚተነትኑት በላይ ሁኔታው አንዳንድ የወያኔ መሪዎች የሚይዙት የሚለቁት አሳጥቷቸዋል ማለት ነው። ነገር ግን ደግሞ ከዚህ ውጥረት ሽብርን በመፍጠር እንወጣለን ካሉ እነዚህ የወያኔ መሪዎች የሚከተሉት የእብዶች ሎጅክ ነው ከማለት ሌላ ምንም መጨመር አይቻልም። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በወያኔ በራሱ ውስጥ የአጥፍቶ መጥፋት ፖሊስን በሚከተሉና ለሃገሪቱ ችግሮች ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስቀድሙ መፍትሄዎችን በሚሹት ኃይሎች መሃከል ያለውን ቅራኔ ያባብሰዋል እንጂ አያረግበውም። በጸረ ወያኔ ትግል በተሰማሩት ኃየሎችም አካባቢ የሚደረገውን ሁለገብ ትግል ይበልጥ የሞት ሽረት ተጋድሎ መልክ እየሰጠ ያጎለብተዋል እንጂ በምንም ዓይነት አያበርደውም።

ሁለተኛው የሚሰነዘረው ምክንያት የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ያደርጋሉ ከተባለው ጉብኝት ጋር የተያያዘ ነው። እንደነዚህ ታዛቢዎች ከሆነ የወያኔ አንዳንድ መሪች ዓላማ አቅፋ ድግፋ የያዘቻቸው የአሜሪካ መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ቢያንስ በአዲስ አበባ ደረጃ ከተቃዋሚ የጸዳችና ነጻው ፕሬስ ህዝቡን መቀስቀስ የማይችልባት የተረጋጋች የምትመስል አገር ለማሳየት ይፈልጋሉ።

እንዲህ ዓይነቱ ሎጅክ ደግሞ ከእብደትም እብደት ነው።

መጀመሪያ አንድ ጨርሶ እንግዳ የሚሆን ነገር አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የነጻ ፕሬስ፣ የዲሞክራሲ፣ የሰው ልጅ መብት ግንባር ቀደም ተሟጋች ነኝ የምትል አገር መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ባይሆን በጎደለ እንዲሟላ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል እንጂ ለሳቸው እጅ መንሻ ሲባል ይህ መከረኛ ህዝብ ከወትሮው ይበልጥ የሚንገላታበት፣ ድሮውንም በሞት